Utlendingsdirektoratet
Norwegian Directorate
of Immigration

# በጥገኝነት መቀበያ ማእከል ለሚኖሩ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ

Informasjonsskriv til beboere i asylmottak om stønad – amharisk versjon

# Innhold


በጥገኝነት መቀበያ ማእከል ለሚኖሩ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ..... 3

ገንዘብ የመቀበል መብት አለዎት ..... 3

ተጨማሪ ሽፋን የማግኘት መብት ሊኖርዎት ይችላል ..... 3

ወጭው በቅድሚያ ማመልከት ሳያስፈልግ በጥገኝነት መቀበያ የሚከፈል ነው ..... 3

ወጪዎችዎን ለመሸፈን ማመልከት አለብዎት ..... 4

ተቀናሽ/egenandel (የእርስዎ ድርሻ መጠን) ..... 4

ገንዘቡን ቀደም ብለው ማግኘት ይችላሉ ..... 5

ደንቦች ..... 5

# በጥገኝነት መቀበያ ማእከል ለሚኖሩ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ

በጥገኝነት መቀበያ ማእከል የሚኖሩ የገንዘብ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ።

በዚህ ሰነድ ውስጥ በኖርዌይ በየስደተኞች ዳይሬክቶሬት (UDI) ሊሸፈኑ ስለሚችሉ ወጪዎች መረጃ ያገኛሉ። በጥገኝነት መቀበያ ማእከል ያሉ ሰራተኞች ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡዎት እና ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ካለዎት ሊረዱዎት ይችላሉ።

## ገንዘብ የመቀበል መብት አለዎት

በወር ሁለት ጊዜ መሰረታዊ ኣበል (basisstønad) ይከፈልዎታል። ገንዘቡን በጥሬ ገንዘብ ወይም በካርድ ያገኛሉ። ይህ ገንዘብ በጣም መሠረታዊ ወጪዎችዎን ይሸፍናል።

በመሠረታዊ አበል ምን ያህል ገንዘብ እንደሚቀበሉ የሚወሰነው በሚከተለው ነው

- በምን አይነት የጥገኝነት መቀበያ ማእከል ይኖራሉ
  - የምግብ አገልግሎት በሌለው የጥገኝነት መቀበያ ማእከል የሚኖሩ ከሆነ፣ የምግብ አገልግሎት ባለው የጥገኝነት መቀበያ ከሚኖሩት የበለጠ ገንዘብ ያገኛሉ።
  - በግዚያዊ መቀበያ/transittmottak ወይም በኣስቸኳይ መቀበያ የሚኖሩ ከሆነ፣ በመደበኛ የጥገኝነት መቀበያ ማእከል ከሚኖሩት ያነሰ ገንዘብ ያገኛሉ።
  - በብሔራዊ መጤዎች መቀበያ/ Nasjonalt ankomstsenter ገንዘብ አያገኙም ፡ ነገር ግን እንደ አስፈላጊነቱ ምግብ፣ ንፅህና እቃዎች፣ አሊጋዎች እና አልባሳት ይሰጥዎታል።
- ብቻዎን ወይም ከቤተሰብዎ ጋር ከሆኑ እንዲሁም ልጆች ካሉዎት ዕድሜያቸው
- የጥገኝነት ማመልከቻዎ ሁኔታ
  - የጥገኝነት ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ ወይም ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካላገኘ፣ ከኖርዌይ ለቀው እንዲወጡ ከተወሰነ፣ የሚያገኙት ገንዘብ ይቀንሳል።
- የራስዎ ገንዘብ ወይም ዋጋ ያለው ነገር ካሉዎት። ንብረት ወይም ገቢ ካሉዎት ለጥገኝነት መቀበያ ማእከል ሰራተኞች ማሳወቅ አለብዎት።

## ተጨማሪ ሽፋን የማግኘት መብት ሊኖርዎት ይችላል

ለመሰረታዊ ኣበል የሚሰጥ ገንዘብ (basisstønad) በጣም መሠረታዊ ወጪዎችዎን ለመሸፈን የታሰበ ነው፡ ሆኖም ሌሎች ወጪዎችን ለመሸፈን ድጋፍ የማግኘት መብትም አለዎት። ይህ ተጨማሪ ድጋፍ (tilleggsstønad) ተብሎ ይጠራል።

ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ በሁለት የተለያዩ መንገዶች ማግኘት ይችላል:

1. ወጭው በቅድሚያ ማመልከት ሳያስፈልግ በጥገኝነት መቀበያ የሚከፈል ነው። የእርስዎ ወጪ ለመሸፈን ኣስፈላጊ ከሆነ፡ በጥገኝነት መቀበያ የሚሰሩ ሰራተኞች ያነጋግሩ።
2. ወጪውን ለመሸፈን ለUDI/ለኖሮዌይ የስደተኞች ዳይሬክቶሬት ማመልከት አለብዎት። በሚኖሩበት የጥገኝነት መቀበያ ለ UDI ማመልከቻ እንዲያቀርቡ ይረዳዎታል። ምላሽ እስኪያገኙ ድረስ መጠበቅ አለብዎት ወጪው እንደሚሸፈኑ ለማወቅ።

### ወጭው በቅድሚያ ማመልከት ሳያስፈልግ በጥገኝነት መቀበያ የሚከፈል ነው

በጥገኝነት መቀበያ የሚኖሩ የሚወሰነው በሚከተለው ነውየሚወሰነው በሚከተለው ነውውን ወጪዎች ይሸፍናሉ

- ለሥነ ልቦና ባለሙያ፣ ለሥነ-አእምሮ ሐኪም እና ለፊዚዮቴራፒ፡ የአእምሮ ጤና ሕክምና አካል በሚሆንበት ጊዜ። ከህክምና ጋር በተያያዘ መድሃኒቶች እና አስፈላጊ መጓጓዣዎች መድሃኒቶች እና አስፈላጊ መጓጓዣዎች በተጨማሪም ይሸፈናል።
- በመዋለ ሕፃናት ትምህርት ቤት ወይም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚጀምሩ ሕፃናት መሳሪያዎች፣ እስከ ተወሰነ መጠን ወጪ።

- የአንድ ጊዜ ድጎማ የማግኘት መብት ከሌለዎት፡ እስከ ተወሰነ መጠን ድረስ በወሊድ ጊዜ ለሚፈጸሙ ወጪዎች[1]

በመጤዎች መቀበያ ማእከል/ankomstsenter፣ በግዚያዊ መቀበያ/transittmottak ወይም ብኣስቸኳይ መጠለያ የሚኖሩ ከሆነ የሚከተሉት ወጪዎች ይሸፈናሉ

- አስፈላጊ የጤና ወጪዎች እንደ በሐኪም የታዘዙ መድሃኒቶች፣ ወደ ሐኪም ወይም ሆስፒታል ለመሄድ
- ኣስቸኳይ የጥርስ ሕክምና
- ከአስፈላጊ የጤና ህክምና ጋር በተያያዘ የመጓጓዣ ወጪ
- ዝግጁ የሆነ የዓይን መነፅር/ferdigbriller

በውህደት መቀበያ/ integreringsmottak የሚኖሩ ከሆነ የሚከተለውን ወጪዎች ይሸፈናሉ

- በውህደት ተኮር እርምጃዎች ለመሳተፍ ለወርሃዊ የህዝብ ማመላለሻ /መጓጓዣ ወጪዎች።

## ወጪዎችዎን ለመሸፈን ማመልከት አለብዎት

በተራ የጥገኝነት መቀበያ የሚኖሩ ከሆነ ወጪዎችን ለመሸፈን ማመልከት አለብዎት

- ለጤና አገልግሎቶች
- በሐኪም ለታዘዙ መድኃኒቶች
- ለጥርስ ሕክምና።

በጥገኝነት መቀበያ የሚኖር ማንኛውም ሰው የሚከተሉት ወጪዎች ለመሸፈን ማመልከት ይችላል፣

- የእይታ ምርመራ እና መነጽር ከአይን ሐኪም፣ ወይም በዕለት ተዕለት ሕይወት ለመስራት የሚያስፈልጉዎት ሌሎች መሳሪያዎች
- አስፈላጊ የጥርስ ህክምና
- አስፈላጊ የመጓጓዣ ወጪዎች
- ከመደበኛው በላይ አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ልብሶች እና መሳሪያዎች
- በጥገኝነት መቀበያ ማእከል የእሳት አደጋ ወይም ሌሎች አደጋዎች ሲከሰቱ የጠፉ ንብረቶችን ለመተካት
- በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ዩኒቨርሲቲ ወይም ኮሌጅ ለትምህርት የሚሆን መሳሪያዎች
- በማንነት ጥርጣሬ ምክንያት የተወሰነ የመኖሪያ ፈቃድ ካለዎት፡ የመታወቂያ ሰነዶችን ለማግኘት ለሚደረጉ ወጪዎች
- የቀብር ሥነ ሥርዓት ማስፈጸሚያ።

## ተቀናሽ/egenandel (የእርስዎ ድርሻ መጠን)

በተራ የጥገኝነት መቀበያ ማእከል በሚኖሩበት ጊዜ፡ ለጤና ሕክምና፣ ለጥርስ ሕክምና እና ለመሳሰሉት እንደ መነፅር ያሉ ለአስፈላጊ መሣሪያዎች ወጪዎች ከመሸፈንዎ በፊት፡ በዓመት የተወሰነ መጠን መክፈል አለብዎት። ይህ የመጠን ገደብ/ beløpsgrense ይባላል።

ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ ወይም ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካላገኘ የመጠን ገደብ የለዎትም።

[1] folketrygdloven § 14-17.

## ገንዘቡን ቀደም ብለው ማግኘት ይችላሉ

ተቀናሹ መጠን ከመድረሱ በፊት፡ ወጪዎችን ለመክፈል እርዳታ ከፈለጉ፡ ለሽፋን ማመልከት አለብዎት፣ እርስዎ ከሚቀበሉት ጊዜ ቀደም ብለው የክፍያውን የተወሰነ ክፍል ለመቀበል ማመልከት ይችላሉ (የእርስዎ መሠረታዊ አበል ቅድመ ክፍያ/ basisstønaden)። ነገር ግን በሚቀጥለው ክፍያ ያነሰ ገንዘብ ይቀበላሉ (መሰረታዊ ኣበል/ basisstønaden ዝቅተኛ ይሆናል)። በዚህ መንገድ የተቀበሉትን ቅድመ ክፍያ መልሰው ይከፍላሉ።

እንዲሁም አንድ ኣስፈላጊ ነገር ለመግዛት እርዳታ ከፈለጉ ወይም ቀድሞ ከተጠቀሱት ሌሎች አስፈላጊ ወጪዎችን ለመክፈል ከፈለጉ፡ አስቀድመው ማመልከት ይችላሉ።

## ደንቦች

በጥገኝነት በመቀበያ ማእከል በሚቀመጡበት ጊዜ ገንዘብ የማግኘትዎ ሙብትዎ እና ያለብዎት ግዴታዎች፡ በመቀበያ ማእከል ነዋሪዎች በሚመለከት ደንቦች ይወሰናል። ይህን ደንብ በድህረ-ገፅ www.udiregelverk.no ማግኘት ይችላሉ። እዚህ በተጨማሪበመክፈት UDI 2024-002-V1 ታገኛላችሁ፣ ዝርዝር መረጃ እና መሰረታዊ ፍላጎት የሚሰጥ እርዳታ ለመተመን የሚውል ምጣኔ በሙቶኛ ወይ ደረጃ ማግኘት ይቻላል። እሱም ለመሠረታዊ አበል የትኞቹ ተመኖች እንደሚተግበሩ (ምን ያህል ገንዘብ እንደሚቀበሉ) ያሳያል።